የተማሪ ስም:_____ የትምህርት ዓይነት: አማርኛ
ክፍል: 8 ምደባ: _____ መንፈቅ: 1ኛ መለማመጃ 3
ቁጥር :_____ ቀን: ታህሳስ /2016 ዓ.ም

ምንባብ

ወርቅነህ እሸቴ ወይም ዶክተር ቻርልስ በ 1857 ዓ.ም ከአባታቸው ነጋድራስ እሸቴ እና ከእናታቸው ከወ/ሮ ደስታ ወ/ማርያም በጎንደር ከተማ ተወለዱ። አፄ ቴዎድሮስ በ 1860 ዓ.ም አእምሮአቸው በቁጣ እየታወከ፤ የወቅቱ ሁኔታ ካቀዱት ጋር አልጣጣም ቢላቸው የጎንደር ካህናትና ታላላቅ ሰዎችን እያሰሩ በግዞተኝነት ወደ መቅደላ መላክ ጀመሩ። በዚህ ጊዜ ነጋድራስ እሸቴም ታስረው ወደ መቅደላ ተወስደው ነበር። ሚስታቸው ወ/ሮ ደስታም ታስረው ወደ መቅደላ ተወስደው ነበር። ሚስታቸው ወ/ሮ ደስታም እንዲሁ አንድ ልጃቸውን ወርቅነህን ይዘው ወደ መቅደላ በግዞት ሔደው ተቀመጡ።

በ 1860 ዓ.ም በሚያዝያ ወር እንግሊዞች አፄ ቴዎድሮስን ወግተው መቅደላን ሲይዙ ህፃኑ ወርቅነህ እሸቴ እድሜያቸው የሁለት ዓመት ከመንፈቅ ልጅ ነበሩ። በዚህ ወቅት እንግሊዞች በመቅደላ ኮረብታ ሲገቡ ሽብር ሆነና ሁሉም ራሱን ለማዳን ሽሽት ያዘ። በዚህን ጊዜ ወርቅነህ እሸቴ ብቻቸውን በአንድ ቤት ቀርተው ነበርና የእንግሊዝ ወታደሮች ህፃኑ ወርቅነህን ባገኟዋቸው ጊዜ አዝነው ወደ ጦር አለቃ ወስደው አስረከቧቸው።

እንግሊዞች ከመቅደላ የዘረፏቸውን ቅርሶችና የተለያዩ ንዋየ ቅድሳት ይዘው ወደ ሀገራቸው ሲመለሱ እቴጌ ጥሩወርቅን፣ ልጃቸው ልኡል ዓለማየሁን እንዲሁም ወርቅነህ እሸቴን ይዘው ወደ ጠረፍ እየተጓዙ ሳለ እቴጌ ጥሩወርቅ ገና ጠረፍ ሳይደርሱ ታመው ሞቱ። ከባህር ወደቡ ሲደርሱም ዓለማየሁ ቴዎድሮስ እና ወርቅነህ እሸቴ ተለያዩ። ጀኔራል ሮበርት ናፒየር ጠረፍ ሲደርስ ወደ እምግሊዝ ሀገር ስለተጠራ ልኡል ዓለማየሁን ይዞ “H.M.S force” በሚባለው መርከብ ተሳፍሮ ወደ እንግሊዝ አመራ። ህፃን ወርቅነህ እሸቴ ደግሞ ከኮሎኔል ቻርልስ ቸምበርሊን ጋር በመሆን ወደ ህንድ አቀኑ።

እንግሊዛዊው ኮሎኔል “ቻርልስ” የተባለውን የራሱን ስም ለብላቴናው ወርቅነህ እሸቴ በመስጠት ወርቅነህ ስማቸው ቻርልስ እየተባሉ ይጠሩ ጀመር። በህንድ ሀገር ከአሳዳጊያቸው ጋር መኖር የጀመሩት ወርቅነህ እሸቴ ለአራት ዓመታት ያህል በህንድ እንደቆዩ አሳዳጊ አባታቸው ኮሎኔል ቻምበርሊን ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። ይሔኔ ኮሎኔል ማርቲን የተባለው ኦፊሰር ፑንጃብ ውስጥ ከአንድ የሚሲዮን ትምህርት ቤት አስገቧቸውና ትምህርታቸውን በዚያው እየተከታተሉ አደጉ።

ወርቅነህ እሸቴ ፑንጃብ ላይ እየተማሩ ካደጉ በኋላ በመንግስት ክፍል ሲቪል ዶክተር ሆነው ይሰሩ ጀመር። ወደ ፑንጃብ ዩኒቨርሲቲም በመግባት ጎበዝ ከሚባሉ ተማሪዎች መካከል ሐኪም ወርቅነህ አንዱ ለመሆን ጊዜ አልወሰደባቸውም። በመጨረሻም በህክምና ሙያ ተመርቀው በረዳት ሐኪምነት ስራቸውን ቀጠሉ፤ እያደረም በቀይ ጥገና ሙያቸው በህንዶች ዘንድ ተወዳጅ እየሆኑ መጡ። ለሁለት ዓመት ያህል ካገለገሉ በኋላም ከፍተኛ ትምህርት ለመከታተል ከህንድ ወደ እንግሊዝ ተጓዙ።

በ 1889 ዓ.ም ወደ እንግሊዝ ሔደው በኤድንብራና በጎስጎው ዩኒቨርሲቲ ህክምና ተምረው በቀዶ ጥገና ሙያ በታላቅ ማዕረግ ተመረቁ። ሲመረቁም ከሐኪሞች ማህበር “የመጀመሪያው ባለ አንጎል ጥቁር ሐኪም” የሚል የምስክር ወረቀትና መቀስ ተሸለሙ።እ.ኤ.አ. በ 1891 ዓ.ም በ 36 ዓመታቸው ህንድ ግዛት ወደ ነበረችው ወደ በርማ ተላኩ። በትውልድ ኢትዮጵያዊ ዜግነት እንግሊዛዊው ዶክተር ቻርልስ ማርቲን በእንግሊዝ የህክምና ተቋም ውስጥ የሰሩ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ የህክምና ባለሙያ ለመሆን በቁ።

ምንጭ (ፍፁም ወ/ማርያም ያልተዘመረላቸው፤ ሐኪም ወርቅነህ እሸቴ ገፅ 37-39 2003 ዓ.ም)

መመሪያ አንድ፡- <u>ከዚህ በታች የቀረቡት የምንባብ ጥያቄዎች አራት አራተ አማራጭች ይዘዋል ምንባቡን በጥሞና በማንበብ ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልስ(ሽ)።</u>

1. አፄ ቴዎድሮስ የጎንደር ካህናትና ታላላቅ ሰዎች ወደ መቅደላ መላክ የጀመሩት ለምንድን ነው?
   ሀ. ሰዎቹ ስላስቸገሩ ለ. በሁኔታዎች አስገዳጅነት።
   ሐ. የወቅቱ ሁኔታ ካቀዱት ጋር ስላልተጣጣመ መ. መልሱ አልተሰጠም።
2. በሶስተኛው አንቀፅ የመጨረሻው መስመር “አቀኑ” ለሚለው ቃል ፍቺ የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. አስተካከሉ ለ. ሔዱ ሐ. ቅናት ያዛቸው መ. አሳደጉ
3. ሐኪም ወርቅነህ ፑንጃብ ሚሲዮን ውስጥ ያስገባቸው ማነው?
   ሀ. ኮሎኔል ማርቲንን ለ. ኮሎኔል ቻርልስ ሐ. ጀኔራል ሮበርት መ. ሀሩሐ መልስ ናቸው
4. ሐኪም ወርቅነህ እሸቴ መጀመሪያ ሲሰሩ የነበረው ምንድን ነው?
   ሀ. በመንግስት ክፍል ሲቪል ዶክተር ሆነው

ለ. በኢደንበራ ዩኒቨርሲቲ መምህር ሆነው
ሐ. በርማ ውስጥ ዶክተር ሆነው
መ. በፑንጃብ ዩኒቨርስቲ ጎበዝ ሀኪም ሆነው

5. ሐኪም ወርቅነህ በስንት ዓመታቸው የምስክር ወረቀት እና መቀስ ተሸለሙ?
ሀ. በ 35 ለ. በ 36 ሐ. በ 34 መ. በ 32

6. ሐኪም ወርቅነህ ፑንጃብ ውስጥ ሚሲዮን ትምህርት ቤት የገቡት በምን ምክንያት ነው?
ሀ. አሳዳጊ አባታቸው በሞት ስለተለዩ
ለ. ኦፊሰሩ በጣምስለሚወዳቸው
ሐ. ዶክተር ለመሆን ስለፈለጉ
መ. ከኢትዮጵያ የሔዱ ስደተኛ ስለሆኑ

7. ይህ ድርሰት የተፃፈው በየትኛው የድርሰት ዓይነት ነው?
ሀ. በገላጭ ለ. በትረካ ሐ. በስዕላዊ መ. በአመዛዛኝ

8. እንግሊዞች መቅደላን የያዙት በስንት ዓ.ም ነው?
ሀ. በ 1857 ለ. በ 1860 ሐ. በ 1863 መ. በ 1889

9. በአጠቃላይ ድርሰቱ ስንት አንቀጾች አሉት?
ሀ. ስድስት ለ. አምስት ሐ. ሰባት መ. ስምንት

10. የአምስተኛው አንቀጽ አጠቃላይ ሃሳብ የሚያተኩረው ምን ላይ ነው?
ሀ. የሐኪም ወርቅነህን አስተዳደግ።
ለ. የሐኪም ወርቅነህን ወደ ትምህርት ዓለም መቀላቀል።
ሐ. የሐኪም ወርቅነህን ከፍተኛ የትምህርት አቀባበል እና ሥራ
መ. መልሱ አልተሰጠም።

መመሪያ ሁለት፦ <u>ለሚከተሉት ጥያቄዎች አራት አራት አማራጮች ቀርበዋል ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ እንደ አጠያየቃቸው መልስ(ሺ)።</u>

11. የማንኛውም ቋንቋ መዋቅር መሰረቱ ነው።
ሀ. ቃል ለ. ሀረግ ሐ. ድምፅ መ. ዓ/ነገር

12. ‹‹ የበሬው ቆዳ ለቦርሳ መስሪያነት እንዲያገለግል ሆኖ <u>ለፋ</u> ።›› የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍቺ የሚሆነው የቱ ነው?
ሀ. ደከመ ለ. ለሰለሰ ሐ. ተገፈፈ መ. ተቆረጠ

13. ስለአንድ ነገር ምንነት ፣አሰራር ፣ ጠቀሜታ ወዘተ የሚያስረዳ የድርሰት አይነት የቱ ነው?
ሀ. ስዕላዊ ድርሰት ለ. አመዛዛኝ ድርሰት ሐ. ገላጭ ድርሰት መ. ተራኪ ድርሰት

14. ‹‹ሳራ ምሳዋን በላች።›› የሚለው ዓ.ነገር የተነገረበት የጊዜ አይነት ከሚከተለው አማራጭ ውስጥ የቱ ነው?
ሀ. የሩቅ ኃላፊ ጊዜ ለ. የቅርብ ኃላፊ ጊዜ ሐ. የትንቢት ኃላፊ ጊዜ መ. የዋህ ኃላፊ ጊዜ

15. ---------- ሁለት ሰዎች ወይም ቡድኖች መካከል የሚደረግ ስርዓት ያለው ሙግት ነው።
ሀ. ጭውውት ለ. ክርክር ሐ. ውይይት መ. ንግግር

16. ከሚከተሉት ውስጥ ስለ ድርብ ቃል ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?
ሀ. ድርብ ቃልን ለመመስረት ሁለት የተለያዩ ቃላት ያስፈልጉናል
ለ. ድርብ ቃልን የምንመሰርተው በንዑስ ሰረዝ ብቻ ነው
ሐ. ድርብ ቃል ሁለት የተለያዩ ቃላት ሁለት ቃልን የሚመሰረቱበት ነው
መ. ለ እና ሐ መልስ ናቸው

17. ‹‹ሰሚራ የገዛችው <u>የሚድ በግ</u> ትላንት ታረደ።››የተሰመርበት የሀረግ አይነት ከሚከተሉት ውስጥ የቱ ነው?
ሀ. ስማዊ ሀረግ ለ. ግሳዊ ሀረግ ሐ. ቅፅላዊ ሀረግ መ. መስተዋድዳዊ

18. ከሚከተሉት ሐረጋት ውስጥ ለግሳዊ ሐረግ ምሳሌ ሊሆን የሚችለው የትኛው ነው ?
ሀ. ፈጥኖ ደረሰ ሐ. በጣም የዋህ
ለ. ቀይ ሀር ምንጣፍ መ. ከቤት ወደ

19. “መዳር” የሚለው ቃል ጠብቆ ሲነበብ የሚኖረው ፍቺ የትኛው ነው?
ሀ. ማግባት ለ. መጋባት ሐ. ማደር መ. መሸምገል

20. ጠብቆና ላልቶ ሲነበብ ሁለት ፍቺ የማይሰጠው ቃል የቱ ነው?
ሀ. በርካታ ለ. ቁጥር ሐ. ደረሰ መ. ነፃ

21. አለማዝ ልጇን <u>ስለገረፈችው</u> በተሰመረበት ቃል ውስጥ “እሷ የሚለውን ባለቤት የሚያሳየው ቅጥያ የቱ ነው?
ሀ. ስለ- ለ. -ኧች ሐ. -ው መ. - -ኧችው

22. ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ ግብፃዊያኑ የሚለው ቃል በትክክል ተነጣጥሎ የሚታየው በየትኛው ነው?
ሀ. ግብፅ - ዊ - ያን - ኡ ሐ. ግብፃ - ዊ - ያኑ

ለ. ግብፅ - አዊ - ያኑ መ. ግብፅ - ኣዊ - ያን - ኡ

23.<< ዝግ >> የሚለው ቃል ጠብቆ የሚነበበው በየትኛው አረፍተ ነገር ውስጥ ነው?

ሀ. ዝግ ብለህ ሂድ ለ. በሩ ዝግ ነው

ሐ› ልጅቱ ዝግ ናት ፣ አትናገረም መ. ኮሚቴው ዝግ ስብሰባ አደረገ

24.ከሚከተሉት ዓ.ነገሮች ውስጥ የቁጥር አለመስማማት ችግር ያለበት የትኛው ነው?

ሀ. አቶ አየለ ከመስክ ስራው ትናንት ተመለሰች።

ለ. እናንተ ስራችሁን በአግባቡ አልሰራንም።

ሐ. ልጆቹ ጎበዝ ተማሪዎች ነው።

መ. በርትቶ ካጠና ጥሩ ውጤት ታመጣለህ።

25.ከሚከተሉት ዓ. ነገሮች ውስጥ ትክክለኛ የስርዓት ነጥብ አጠቃቀም ያለው የቱ ነው?

ሀ. አባቴ "ውጤት እንዴት ነው"? ብሎ ጠየቀኝ።

ለ. " አባቴ ውጤት እንዴት ነው?" ብሎ ጠየቀኝ።

ሐ. "አባቴ ውጤት እንዴት ነው" ብሎ ጠየቀኝ?

መ. አባቴ " ውጤት እንዴት ነው?"ብሎ ጠየቀኝ።

26.ቁርስ አልበላሁም ፤ _____ የርሀብ ስሜት አልተሰማኝም። ክፍት ቦታውን ሊያሟላ የሚችለው አያያዥ የትኛው ነው?

ሀ. ስለዚህ ለ.በመሆኑም ሐ. ይሁን እንጂ መ. እንጂ

27.ከሚከተሉት ውስጥ የቃላዊ ግጥም ባህርይ ያልሆነው የትኛው ነው ?

ሀ. የህዝብ ሀብት ነው። ሐ. የሚተላለፈው በቃል ነው።

ለ. የመለዋወጥ ባህርይ አለው መ. ደራሲው ተለይቶ ይታወቃል።

28.ደኖቻችን በሚለው ቃል ውስጥ ያሉት ቅጥያዎች ከዩዘት አንፃር _____ ያመለክታሉ።

ሀ. አይነትንና መጠንን ሐ. ባለቤትነትን እና እምርነትን

ለ. ብዛትንና ባለንብረትነትን መ. ባለቤት እና ተሳቢ

29.<< ግብርና <u>የትጉህ</u> ሰው ስራ ነው ። >> በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ምሳሌነቱ በየትኛው ሃረግ ነው?

ሀ. በግሳዊ ለ. በቅፅላዊ ሐ. በመስተዋድዳዊ መ. በስማዊ

30.<<እባብ ለእባብ----------።›› የሚለውን ምሳሌያዊ አነጋገር ሊያሟላ የሚችለው አማራጭ የቱ ነው ?

ሀ. ይተያያል ካብ ለካብ ሐ. ይጣላል ያለግባብ

ለ. ይኖራል በአግባብ መ. ለ እና ሐ መልስ ናቸው

31.ሁለት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ነገሮችን (ጉዳዮችን) በማምጣት ስለምንነታቸው ልዩነታቸው እና ተመሳሳይነታቸው የሚያትት የድርሰት አይነት ---------- ይባላል።

ሀ. ተራኪ ድርሰት ሐ. ስዕላዊ ድርሰት

ለ. አመዛዛኝ ድርሰት መ. አስረጂ ድርሰት

32.በአማርኛ ቃላት የአበዛዝ ስርአት መሰረት ነጠላ የሆኑ የመጨረሻ ሆሄያቸው ሳድስ የሆኑ ስሞችን ለማብዛት የምንጠቀምበት ምዕላድ የቱ ነው ?

ሀ. -ኦች ለ.-ዎች ሐ. -ኡ መ. -ኣችን

33.ከሚከተሉት ውስጥ የቢጋር ጠቀሜታ ያልሆነው የቱ ነው ?

ሀ. የድርሰትን መሣሪያ ስልት ይወስናል ለ. የሀሳብ ቅደም ተከተል እንዳይዛባ ይረዳል

ሐ. የሚዘነጋ ሀሳብ እንዳይኖር ያደርጋል መ. የድርሰትን አቅም ያሳይልናል

34.----------ጥልቅ የሆነ የማሰብ ችሎታ ለማዳበር እና ነገሮችን በቀላሉ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር የሚረዳ ጥበብ ነው።

ሀ. ድርሰት ለ. ቃል ሐ. ቅኔ መ.ልቦለድ

35.በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሰረቱ ታሪኮች ላይ ተመስርቶ የልቦለድ አጣፋፍ ስርዓትን ተከትሎ የሚቀርበው የቱ ነው ?

ሀ. ልቦለድ ለ. ኢ-ልቦለድ ሐ. ረጅም ልቦለድ መ. አጭር ልቦለድ

36.----------ደራሲው ታሪኩን የሚያቀርብበት የትረካ አቅጣጫ ነው።

ሀ. ትልም ለ.አንግር ሐ ግጭት መ.መቼት

37.ከሚከተሉት ዓ.ነገሮች ውስጥ ቀጥተኛ ተሳቢ የሌለው ዓ.ነገር የቱ ነው ?

ሀ. ቤቱ በጣም ሰፊ ነው። ሐ. ግንበኞቹ ህንፃውን አፈረሱት።

ለ. ህፃኑ ብርጭቆውን ሰበረው። መ. ወታደሮቹ አስፈሪውን አውሬ ገደሉት።

38.....በልቦለድ ታሪክ ውስጥ ድርጊቱ የሚፈፀምበትን ግዜ እና ቦታ ይገልፅልናል።

ሀ. መቼት ለ. ታሪክ ሐ. ገፀ-ባህሪ መ. ትልም

39.ለስንዴ ይታጨዳል ካልን ለጥጥ ---------- እንላለን።

ሀ. ይቆረጣል ለ. ይለቀማል ሐ.ይሰበራል መ. ይሸለቀቃል

40.በመነሻውና በመድረሻው ላይ ቅጣይ ምዕላዶች የሌሉት ቃል የቱ ነው?

ሀ. አልመጣም ለ. አስተባበረ ሐ. አውራሪስ መ. አይበላም

41.ከሚከተሉት ውስጥ በትርጉም ልዩ የሆነው ቃል የቱ ነው ?

ሀ. ህፀፅ ለ. ችግር ሐ. እንከን መ. ክፋት

42.<<ሰውዬው <u>የወንበር</u> ፍቅር ለሞት ዳረገው።>> የተሰመረበት ቃል ፍካሬያው ፍቺ የሆነው የቱ ነው ?

ሀ. መቀመጫ ለ. ማረፊያ ሐ. ስልጣን መ. ሀእና ለ

43.ከሚከተሉት ውስጥ ገቢር ግስ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ልጁ ብርጭቆ ሰበረ። ለ. ልጁ እግሩ ተሰበረ።

ሐ. ልጁ ብርጭቆ ሰባበረ። መ. ሀ እና ሐ መልስ ናቸው።

44.<<ብዙ ለመግዛት ካሰብኩኝ በኃላ

መገዛኜ መለስኩት ያንን የሰው ገለባ።>> በሚለው ሰምና ወርቅ ቅኔ ውስጥ ወርቁ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. የሰው ገለባ ለ. ገለባ ገዛሁ ሐ. የማይረባ ሰው መ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው።

45.የሀረግን መጠሪያ የሚወስነው _____ ነው።

ሀ. በውስጡ የሚገኙት ቃላት ለ. መሪው ሐ. ተጣማሪዎቹ መ. ገላጩ ቃል

46.የንግግር ክህሎትን ለማዳበር ከምንጠቀምባቸው ተግባራት መካከል የማይካተተው የቱ ነው?

ሀ. የዕሁፍ ሪፖርት ለ. ጭውውት ሐ. ክርክር መ. ውይይት

47.<<አድሮ ቃርያ >> ለሚለው ፈሊጣው አነጋገር ፍቺ የሚሆነው የቱ ነው?

ሀ. የማይበላ ለ. የማይሻሻል ሐ. የሚያቃጥል መ. ያልበሰለ

48. <<ምን አይነት ቄስ ናቸው ተስካር የለመዱ፤

አስታርቁኝ ብላቸው ፍታት ብለው ሄዱ።>> በሚለው ሰም እና ወርቅ ሀብረ ቃሉ_____ ነው።

ሀ. አስታርቁኝ ለ. ብለው ሄዱ ሐ. ብላቸው መ. ፍታት ብለው

49. _____ <<እየ->> በመነሻ እና <<ነው>> በመድረሻ የሚወስድ የጊዜ አይነት ነው።

ሀ. የትንቢት ለ. የአሁን ሐ. የሩቅ ኃላፊ መ. የቅርብ ኃላፊ

50. _____ብቻቸውን ሆነው ሙሉ መልዕክትን ማስተላለፍ የሚችሉ ባለትርጉም የመጨረሻ ቅንጣቶች ናቸው።

ሀ. ነፃ-ምዕላድ ለ. ቃል ሐ. ሐረግ መ. ለ እና ሐ መልስ ናቸው።

51. ከሚከተሉት ውስጥ የአማርኛ የቃል ክፍል ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. ተውሳከ ግስ ለ. መስተዋድድ ሐ. መስተፃምር መ. ግስ

52.ከሚከተሉት ለእርባታ ምዕላድ ምሳሌ ሊሆን የሚችለው የቃል ጥምረት የቱ ነው?

ሀ. ገበዝ-ገበዙ ለ. ሀይል- ሀይለኛ ሐ. ሰው-ሰውነት መ. መርዝ-መርዛማ

53. “ጥጆች” በሚለው ቃል ውስጥ ያለው ቅጥያ ምንን ያመለክታል?

ሀ. ቁጥርን ለ. ፆታን ሐ. መደብን መ. ተግባርን

54. “አንባቢያን” በሚለው ቃል ውስጥ ብዙ ቁጥርን የሚያመለክተው ቅጥያ የቱ ነው?

ሀ. -ን ለ. -ያን ሐ. -ቢያን መ. -ኣን

55. <<ሁለት እግር አለኝ ተብሎ _____ ።>> ይህን ጅምር ምሳሌያዊ አነጋገር ከሚከተሉት በየትኛው መቋጨት ይቻላል?

ሀ. ሁለት መኪና አይነዳም ሐ. ሁለት ዛፍ ላይ አይወጣም

ለ. ከአቅም በላይ አይሮጥም መ. ሁለት ኳስ አይመታም

መመሪያ ሁለት፡ ከስር የቀረበውን ግጥም መሰረት በማድረግ ከተራ ቁጥር **56-60** ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን ምላሽ በመምረጥ መልሱ።

<u>ግጥም</u>

ቀረ መፈረጅ፣

መቀጥቀጥ ሙያ ነው ለጠነከረ እጅ።

ዝገቱን በማራገፍ ብረቱ ሲቀላ፣

አቃጥሎ አገላብጦ መንቀል ነው ሲላላ።

ወናፍ ሲያናፋ እሳት ሲንበለበል፣

የነጠረ ይወጣል የዘቀጠ ከሰል።

56. በመጀመሪያው ስንኝ ክፍት ቦታ ላይ ሊገባ የሚችለው ትክክለኛ ሀረግ ከሚከተሉት የቱ ነው?

ሀ. የወንድ የሴት እያሉ ሐ. የወንድ የሴት ብሎ

ለ. የወንድ እንዲሁም የሴት መ. የወንድ የሴት

57. የሁለተኛው ስንኝ መነሻ ሀረግ ከሚከተሉት ውስጥ የትኛው ነው?

ሀ. መቀጥቀጥ ሙያ ነው ሐ. ለጠነከረ እጅ

ለ. መቀጥቀጥ ሙያ መ. ነው ለጠነከረ

58. በግጥሙ በራብዕ የሚጨርሱ ስንኞች ስንት ናቸው?

ሀ. ሶስት ለ. ሁለት ሐ. አምስት መ. አራት

59. የግጥሙ የመጨረሻ ስንኞች ቤት መድፊያ ቃል የቱ ነው?

ሀ. ሲንበለበል ለ. የዘቀጠ ሐ. ከሰል መ. ሲላላ

60. ግጥሙ በስንት አንጓ (አርኬ) የቀረበ ነው?

ሀ. በአራት ለ. በሦስት ሐ. በሁለት መ. በአንድ